# ከእግዚአብሔር ፍቅር


"… እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።" (ኢሳ 48 ፥ 17)

God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. አዘጋጅ መላኩ ትዕዛዙ E-mail – glnlm @ethiogodslove.org

www.ethioGodslove.org 4ኛ ደብዳቤ 2005 እአአ 4th Quarter 2005


ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ ፥ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል ። (ትንቢተ ኢሳይያስ 54 ፥ 13)

# የጸጋ ስጦታዎች

## ለቤተ ክርስትያን ዕድገት

"እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን፤…" (ሮሜ 12 ፥ 6)

"… እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ለራሱ የጸጋ ስጦታ አለው፥ አንዱ እንደዚህ ሁለተኛውም እንደዚያ።" (1 ቆሮ 7፥7)

"በትንቢት ከሽማግሌዎች እጅ መጫን ጋር የተሰጠህን ፥ በአንተ ያለውን የጸጋ ስጦታ ቸል አትበል። (1 ጢሞ 4፥14)

"ስለዚህ ምክንያት እሳት እንደሚያቀጣጥል ሰው፥ እጆቼን በመጫኔ በአንተ ያለውን የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድታነሣሣ አሳስብሃለሁ። (2 ጢሞ 1፥6)

"…እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፤…" (1 ጴጥ 4፥10)

እየሱስ ክርስቶስን የሕይወትህ ጌታ አድርገኸው እንደ ተቀበልኸው ፥ በዚያን ቀን ከእርሱ ጋር የተቀበልኸው፥ ቢያንስ አንድ የጸጋ ስጦታ ተሰጥቶሃል። ቢታወቅህም ባይታወቅህም ይህ ዕውነት ነው። የጸጋ ስጦታ የሚሰጠውም ለግል ጥቅም ብቻ ሳይሆን አካሉ ለሆነችው ፥ ለቤተ ክርስቲያን መታነፅና በረከት ነው። ይህንንም ጌታ በሕይወትህ ውስጥ ያሰቀመጠውን የጸጋ ስጦታ ተረድተህ ስትሠራበት በቤተ ክርስቲያን በሚያስደንቅ ፍጥነት ታድጋለች።

"ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀ መዛሙርቴ ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይከብራል፡"
(የዮሐንስ ወንጌል 15፥8)

ይህ መልዕክት ከትልቅ መጽሐፍ ተወስዶ፥ በሁለት ገጽ ተጠቃሎ የቀረበ ነው። ስለዚህ የማብራሪያ እጥረት አለው። ሆኖም መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን በዚህ ወቅት የሚለውን ወደ ቅዱሳን ለማድረስ አቅማችን በፈቀደው ማቅረባችን ነው። ተባረኩ።

# የጸጋን ማዕድናት

## ለዓላማው ማውጣት

- <u>የጸጋ ስጦታን አጥርቶ ማወቅ</u>፡–
ጌታ በእኛ ውስጥ ያሰቀመጠው የጸጋ ስጦታ የሕይወታችንን ዓላማ ይወስናል። ይኸውም በመንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዱ አማኝ የሚሰጥና፡– እንደ አካሉ ሁኔታ የሚሠራበት፥ ልዩ ባሕሪ (attribute) ነው። ጸጋና የተፈጥሮ ስጦታ አንድ አይደሉም ምክንያቱም ሁሉም ሰው የተፈጥሮ ተሰጥዖ (talent) ሲኖረው ፥ የጸጋ ስጦታ ግን ያለን አማኞች ብቻ ነን። አማኞችም ሁሉ የመንፈስ ፍሬ ማፍራት ሲጠበቅብን የጸጋ ስጦታ ግን ልዩ ልዩ ነው።

"የጸጋ ስጦታ ልዩ ልዩ ነው፡ መንፈስ ግን አንድ ነው፤አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው፤ …" (1ኛ ቆሮንቶስ 12፥4)

- <u>በጸጋ ስጦታ መሰማራት</u>፡–
ማንኛውም ምዕመን በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ በጎደለ ሥፍራ በጊዜያዊነት ገብቶ ማገልገል አለበት።ነገር ግን <u>ጸጋውን በሚገባ በአገልግሎት ላይ ለማዋልና ተገቢውን ፍሬ ለማግኘት፥ በጸጋው መሰማራት አለበት።</u> በዚያም ልክ፥ አማኝ ሁሉ የጸጋ ስጦታዬ ብሎ የሚሠራበትን መንፈስ መርምሮ ከጌታ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት። ሌላው ደግሞ፥ አንዳንድ ምዕመናን ከአንድ በላይ የጸጋ ስጦታዎች ሊኖራቸው መቻሉ ነው። አንተም ከአንድ ስጦታ በላይ ሊኖርህ እንደሚችል ማሰብ ስሕተት አይሆንብህም። ከሆነም ሁሉንም አውጥተህ ለመንግሥቱ ዕድገት እንድታገለግልበት ጌታ የሚጠብቅብህ መሆኑን አትዘንጋ።

- <u>ጸጋን በፈርሓ እግዚአብሔር መጠቀም</u>፡– <u>በጸጋው ተሰማርቶ የሚያገለግል ሰው ለእግዚአብሔር መንግሥት እንደሚገባ ጠቃሚና ፍሬያማ ይሆናል</u>። ነገር ግን ፍሬው እንዲኖርና እንዲበዛለት፡– ያ ሰው በእርሱ ስለሚሠራው የጸጋ ስጦታ በትኅትና ጌታን ማመስገን እንጂ መታበይ አይገባውም። አንተም በስጦታህ ጌታን ማክበርና ሰዎችን በትኅትና ማገልገል እንጂ መታበይ ደስ አያሰኝህ።

- <u>ጸጋን ያለአግባብ መጠቀም</u>፡–
የጸጋን ስጦታ ለሐብት ማከማቻ፥ሰዎችን ለማጥቂያ ወይም ለግል ክብር መጠቀም ለፍርድ ይዳርጋል። ሌላው መዘንጋት የሌለበት ነገር ደግሞ ፥ በአንዱ ምዕመን የሚሠራው የጸጋ ስጦታ፥በሌሎች ውስጥ ከሚሠራው ጸጋ የማይበልጥ፥የማያንስም መሆኑ ነው። ይህም ያለአንዳች ስጋት፥ ከወንድሞችና ከእህቶች ጸጋ ጋር መተባበር እንደሚቻል ያረጋግጣል። <u>የጸጋ ስጦታ የተሰጠው ለቤተ ክርስቲያን ስለ ሆነ ጋርዮሻዊና ተደጋጋፊ ነው</u>። ከተፈጥሮ ችሎታ የሚለየውም ይኸው ተደጋጋፊነቱ ነው። ስለዚህ በአንተ ውስጥ የሚሠራው የጸጋ ስጦታ ውጤታማነት፡– በወንድሞችና እህቶች ጸጋ ውጤታማነት ላይ የተደገፈ ነው። የሁሉም ግብ የወንጌሉ መሰበክ ስለ ሆነ ፥ እያንዳንዱ በተሰጠው ልዩ የጸጋ ስጦታ ማገልገል እንዲችል ዕድል ሊሰጠው የሚገባውም ለዚህ ነው። ታገልግልና ታፈራ ዘንድ ጸጋን የሰጠህ ጌታ ኢየሱስ ፥ በዚሁ ዓላማ ለወንድሞችና ለእህቶችም የሰጠ ስለሆነ የማንም ጸጋ ተቀብሮ እንዳይቆይ ጌታን መፍራት ይገባል።

- <u>የራስን ልዩ የጸጋ ስጦታ በቶሎ ለይቶ መረዳት</u>፡– የጸጋ ስጦታን ለመቀበል አራት ቅድመ ሁኔታዎች አሉ። እነርሱም፡– <u>1ኛ</u> ጌታ ኢየሱስ የግል አዳኝህና ጌታህ መሆኑ፡– <u>2ኛ</u> በመንፈስ ቅዱስ ሥራ ማመን፡– <u>3ኛ</u> መንፈሳዊ ስጦታህን ለመረዳትና ለመጠቀም የሚያስፈልግውን የበኩልህን ጥረቶች ለማድረግ ፈቃደኛ መሆን፡– <u>4ኛ</u> በጾም በጸሎትና ከኃጢአት በመራቅ ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ መሆን ናቸው።

ለምሳሌ፡– የጸጋ ስጦታንና አሠራሩን አስመልክቶ መጽሐፍ የሚለውን በትጋት ማጥናት ያስፈልጋል። ቤተ ክርስቲያንህ የጸጋ ስጦታን አስመልክቶ ያላትን አቋም ማወቅ። ክርስቲያን ጸሐፊዎች ይህን አስመልክቶ የጻፉትን ማንበብ።በጸጋ ስጦታ በማገልገል ልምድ ያላቸውን ማነጋገርና ምክር መጠየቅ። በሕይወትህ ያለውን ጸጋ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ገልጸ ምክር መጠየቅ። ከዚያም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሻቱ ሲከሰት፡ በሚገኘው ዕድል በተግባር መፈተን። ይህንንም ስታደርግ፡ የትኛው ጸጋ እንዳለህና እንደሌለህ በማስተዋል እየለየህ ትሄዳለህ። ከእያንዳንዱ አገልግሎት በኋላ የሚሰማህን የመንፈስ ቅዱስ ድምፅ አስተውል። የሞከርኸው አገልግሎት በጸጋ ከሆነ መንፈስህ በሐሴት ይሞላል፤ በበረከት ወይም በፍሬ መልክ የሚገለጥ አሉታዊ ውጤት ይታያል። በመጨረሻም አብረውህ ያሉ አገልጋዮች በአንተ ውስጥ ስለሚሠራው የጸጋ ስጦታ የሚያስተውሉትን መስማት ይረዳል።

- <u>ምዕመናን በጸጋ ስጦታቸው ማደግ የሚገባቸውን ያክል እንዲያድጉ ርዳ</u>።የቤተ ክርስቲያንህ መሪዎች፡– ምዕመናን የጸጋ ስጦታቸውን መጠቀም እንዲችሉ የሚያበረታታ፥ግልጽ መመሪያ እንዲከተሉ አደፋፍር፤ ሆን ተብሎ የተዘጋጀ፥ የጸጋ ስጦዎች በተግባር የሚሞከሩባቸው ፥ ዝግጅቶች በቤተ ክርቲያን የአገልግሎት ሰንጠረዥ ውስጥ ይለመድ።<u>ምዕመናን ከቦዘኑና በተሳታፊነት ብቻ ከተተዉ፥የጸጋ ስጦታዎች ሊገለጡ ያዳግታል</u>። እንዲሁም <u>ጸጋቸውን በማይጠቀም አገልግሎት ተጠምደው በሥጋ ቢፈረጡ ውጤቱ ያው የሥጋ ፍሬ ይሆናል</u>። ነገር ግን፡– ጌታ መንፈስ ቅዱስ በነፃነት የሕዝቡን ጸጋ ለመግለጽ እንዲመቸው ሁኔታን ማሰናዳት ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም ነው።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አዘውትረው በዚህ ርዕስ ላይ እንዲያስተምሩና እንዲሰብኩ አደፋፍር። በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፥ በሰንበት ትምሕርትና በግለ ጥናት አማካኝነት ምዕመናን በዚህ ጉዳይ ላይ የጠራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግንዛቤና ዕውቀት እንዲኖራቸው ጥረት ይደረግ። ሁኔታው ጤነኛ ከሆነ፥ማንኛውም ምዕመን፥ ጌታን በተቀበለ ከአራት ወር እስከ አንድ ዓመት ባለ ጊዜ ውስጥ፥የጸጋ ስጦታውን ማወቅ እንደሚችል ይታመናል። ስለዚህ፥መሪዎች እያስተማሩ ይህንኑ ውጤት መከታተል ይገባቸዋል። <u>እያንዳንዱ ምዕመን የሌላውን ጸጋ ተገልጦ በሥራ ላይ መዋል በናፍቆት መጠባበቅና ማደፋፈር ይገባዋል። ይህም የቤተ ክርስቲያን ቋሚ ትኩረት መሆን አለበት።</u> በዚህ መልክ የምዕመናን ጸጋ በሙላት የሚሠራባት ቤተ ክርስቲያን ፥ የኃይማኖት መልክ ያላት ደካማ ድርጅት መሆኗ ቀርቶ ፥ የእግዚአብሔር ሕላዌ መገለጫ ትሆናለች።

<u>ይኸም በሐዋሪያት የነበረው፥ የመዳንና ተለውጦ አገልጋይ የመሆን፡– የወንጌል ኃይልና ውበት ነው</u>። እግዚአብሔርም ዓለምን ሲያሸንፍ የኖረው <u>በባሮቹ ውስጥ በሚሠራው ኃይሉ</u> (ጸጋው) እንጂ፥ በየኃይማኖት መልካችን አይደለም።

## ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎች

በሮሜ 12፥ 6-8 እንደ ተመለከተው ፡– የትንቢት፥የአገልግሎት፥የማስተማር፥የመምከር፥የመስጠት፥የመግዛትና(ማስተዳደር) የመማር (ምሕረት) የጸጋ ስጦታዎችን እናነባለን።

በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፥8-11 ደግሞ፦ "ለአንዱ ጥበብን መናገር በመንፈስ ይሰጠዋልና ለአንዱም…እውቀትን መናገር…፥ለአንዱም… እምነት፥ለአንዱም የመፈወስ ስጦታ፥ለአንዱም ተአምራትን ማድረግ፥ለአንዱም ትንቢትን መናገር፥ለአንዱም መናፍስትን መለየት፥ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን መናገር፥ ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም ይሰጠዋል፤ ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል።"ተብሎ የተጻፈውን እናነባለን።

ከዚህ በታች የምንመለከታቸውን ልዩ ልዩ የጸጋ ስጦታዎች በመመልከት :- የቱ ወይም የትኞቹ በአንተ ውስጥ እንደሚሠሩ በጸሎት ጌታን እድትጠይቅ እናሳስባለን። ከዚህ ንባብ የተነሣ፥ አንድም ምዕመን እንኳ ቢሆን ተነቃቅቶ ፥ በሕይወቱ ውስጥ ጌታ ያስቀመጠውን ጸጋ እንሥቶ፥ ሠራተኛ ወደ መሆን እንዲገባ ፀሎታችን ነው።

* **ጃንደረብነት** (celibacy):-ጋብቻን በመተው፥በአገልጋይነት ተወስኖ ለመኖር የሚሰጥ የጸጋ ስጦታ ነው። ይህንን ስጦታ የተቀበሉ ሰዎች ጥቂቶች ሲሆኑ፥ ሌሎች ሰዎች የማይችሉትን ሥጋዊ ፈተና መቋቋም የሚያስችላቸው ይህ ጸጋ ነው። በ1ኛ ቆሮንቶስ 7 ፥ 7 "ሰው ሁሉ እንደ እኔ ሊሆን እወዳለሁና፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ለራሱ የጸጋ ስጦታ አለው፥…" የተባለው ፥ ሐዋሪያው ጳውሎስ ስለ ራሱ አለማግባት የጠቆመበት ክፍል ምሳሌው ነው።

* **የመስዋዕትነት ጸጋ** :- ይህ እስከ ነፍሳቸው ድረስ በቆራጥነት ለመሰዋት ለጥቂቶች የሚሰጥ የጸጋ ስጦታ ነው። ይህም ለጌታ ኢየሱስ ክብርና ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም በታላቅ መስዋዕትነት ውስጥ ለማለፍ የሚያስችል ጸጋ ነው። ለምሳሌ በሐዋሪያት ሥራ 7 እንደተጻፈው፥በእስጢፋኖስ የሠራው ጀግንነት የመስዋዕትነት ጸጋ ነው።

* **እንግዶችን ተቀብሎ የማስተናገድ ጸጋ**:- እንግዶችን በመቀበልና ችግረኞችን በመርዳት፡ ቤተ ክርስቲያንን ለማሳደግ የሚሰጥ ጸጋ ነው።

* **የመማለድ ጸጋ**:- ጌታ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በጸጋ ሞልቶ የሚያስቀምጣቸው፥አዘውትረው ለረዥም ጊዜ የሚቃትቱ፥ ጸሎታቸውም አዘውትሮ መልስ የሚያገኝ ፥ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የሚማልዱ ቅዱሳን የመማለድ ጸጋ intercession ያላቸው ናቸው

* **የአምልኮ መሪነት ጸጋ**:- የመንፈስ ቅዱስን ስሜት በመከተል የሕዝቡን ልብ በሚያስገርም መለኮታዊ አሠራር ከጌታ ጋር በአምልኮ የማገናኘት ጸጋ ነው። እንዲህ ያሉ መሪዎች ለመንፈስ ቅዱስ ምቹ ስለሚሆኑ ጌታ የወደደው ነገር፥ድንቅና መገለጦች በሥፍራው ይከሰታሉ። አምልኮም ደረቅና ለማዳዊ ሥርዓት መሆኑ ቀርቶ፥ በጌታ ሕላዌ (መገኘት) የተሞላና ብሩክ ይሆናል።

* **የመስጠት ጸጋ**:- ይህንን ጸጋ የተቀበሉ፥ ለእግዚአብሔር ሥራና ለድኆች፥ገንዘባቸውንና ንብረታቸውን በደስታ በመስጠት ይታወቃሉ። ይኸውም አማኝ ሁሉ ማድረግ ከሚገባው ከአሥራትና ከመባ በተጨማሪ ነው።

* **የመለየት ጸጋ**:- ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም አንዳንድ ምዕመናን ከእግዚአብሔር የሆነና ያልሆነውን ነገር በእርግጠኝነት ማወቅ ተሰጥቷቸዋል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚታዩ አንዳንድ ግልጽ ያልሆኑ ነገሮች:- ከጌታ ይሁኑ ከሥጋ ወይም ከሴይጣን መሆናቸውን ተረድተው የሚገልጡ ናቸው።

* **አጋንንትን የማስወጣት ጸጋ**:- በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አጋንንትን ለማስወጣት ጌታ ከሌሎች አማኞች በተለየ ጸጋ ያስታጠቃቸው:-ለሌሎች ያልታዘዙ ደፋር አጋንንት ሳይቀሩ ታዝዘው ሰዎችን የሚለቁላቸው ቅዱሳን ይህን ጸጋ የተቀበሉ ናቸው።

* **የማስተማር ጸጋ**:- ለቤተ ክርስቲያን ተአንጾና ጤንነት የሚጠቅም ትምሕርትን በልዩ ጸጋ ለመግለጽ የሚያስችል ስጦታ ነው።

* **የእረኝነት ጸጋ** (Pastor):- የምዕመናንን ጊዜያዊ ሆነ የረዥም ጊዜ መንፈሳዊ ደኅንነት ለመንከባከብ የሚያስችል፥የመጋቢነት ጸጋ ነው።ይህንን ጸጋ የተቀበሉ ሁሉ በፓስተርነት (ቅስና) ቦታ ላይ እንዳልሆኑ ሁሉ፥ ፓስተሮች (ቄሶች) ሁሉም ይህን ጸጋ አላቸው ማለት አይቻልም። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችና ዲያቆናት ከቄሱ የተሻለ የእረኝነት ጸጋ የሚታይባቸው በዚህ ምክንያት ነው።

* **የማጽናናትና የማደፋፈር ጸጋ**:- ምዕመናንን እንዳስፈላጊነቱ የማጽናናትና ወደ መንፈሳዊ ግባቸው እንዲደርሱ የማደፋፈር ጸጋ ነው።

* **የማስተዳደር ጸጋ**:- ምዕመናንን ማደግ በሚገባቸው አቅጣጫ በሚገባ እንዲያድጉ ለመርዳት የሚያስችል፥ የቅርብና የሩቅ ጊዜ ዕቅድ በማውጣትና ፥ በማስተባበር ወደ ስኬት የመምራት ጸጋ ነው።

* **የዕምነት ጸጋ**:- አማኝ ሁሉ ዕምነት አለው። ነገር ግን ለቤተ ጥቅም ልዩ የዕምነት ጸጋ የተሰጣቸው ፥ የወደፊቱን ነገር በጽኑ ርግጠኝነት ማወቅና መግለጽ የተሰጣቸው የዕምነት ጸጋ ያላቸው ናቸው።

* **የመሪነት ጸጋ** :- ይህ ደግሞ ከምዕመናን ለአንዳንዶቹ የሚሠጥ፥ በእግዚአብሔር ዓላማ መሠረት፥ሰለ ወደፊቱ ጉዳዮች፥መመሪያን አውጥቶና ለምዕመናን በቀላሉ በማስረዳት፥ለማስተባበር የሚያስችል ልዩ ጸጋ ነው።

* **የወንጌላዊነት ጸጋ**:- ማንኛውም አማኝ የጌታው ምስክር ለመሆን የተጠራ ነው። ነገር ግን ወንጌልን ሲሰብኩ የብዙ ሰዎችን ልብ ለጌታ የመማረክ (የወንጌላዊነት) ልዩ ጸጋ የተሰጣቸው ጥቂቶች አሉ። አሜሪካዊው ወንጌላዊ ቢሊ ግራም ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ናቸው።

* **የወንጌል መልዕክተኛነት(ሚሲዮናዊነት)** ጌታ የሰጣቸውን ማንኛውንም ጸጋ በመጠቀም፥ከራስ ባሕል ወጥቶ በመሄድ ወንጌልን ለማገልገል የሚያስችል ጸጋ ነው።

* **የሐዋሪያነት ጸጋ**:- በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉት አገልግሎቶች በአንዱ ላይ፥ኃላፊነትን ይዞ፥ፍሬያማ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ልዩ መለኮታዊ ጸጋ ነው። ሐዋሪያነት መንፈስ ቅዱስንና ቃሉን በመከተል ቤተ ክርስቲያን ጤንነቷ እየተጠበቀ፡ ወንጌልን በመስበክ እንድታድግ የሚረዳ የጸጋ ስጦታ ነው።

* **የዕውቀት ጸጋ**:- የቤተ ክርስቲያንን ዕድገትና ደኅንነት ለመጥቀም ከምዕመናን ለአንዳንዶቹ የሚሰጥ፡- መንፈሳዊ ዕውቀትን የማግኘት፥የማብዛት፥ የመመረመርና የመግለጽ ልዩ ጸጋ ነው።

* **የጥበብ ጸጋ**:- በቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች ላይ አንዳንድ ዕውቀቶች እንዴት በሥራ ላይ መዋል እንደሚገባቸው የመንፈስ ቅዱስን ጥልቅ ነገር መረዳት የሚያስችል ልዩ መንፈሳዊ ስጦታ ነው።

* **የርኅራኄ ጸጋ**:- እግዚአብሔር ከምዕመናን ላንዳንዶቹ የሚሰጠው፥በልዩ ልዩ ሁኔታ ለሚጨነቁና ለተቸገሩት ሰዎች የመራራትና የማዘን ፥ እንዲሁም የመርዳት ጸጋ ነው። እነዚህም በዚህ ጸጋ የጌታን ፍቅር በቤተ ክርስቲያንና በውጭ ይገልጣሉ።

* **የመርዳት ጸጋ**:- ማንኛውንም ችሎታቸውን በመጠቀም፥ ምዕመናን በአገልግሎታቸው ለጌታ ሥራ ፍሬያማ እንዲሆኑ ለመርዳት ራሳቸውን መስጠት እንዲችሉ ለአንዳንድ አማኞች የሚሰጥ ጸጋ ነው።

* **የነቢይነት ጸጋ**:- በቤተ ክርስቲያን ሕይወት በየወቅቱ በሚሆኑ ነገሮችና ጉዳዮች ላይ ወቅታዊ መልዕክቶችን ከመንፈስ ቅዱስ ተቀብለው፥ ለሕዝቡ ለሚገልጡ አማኞች የሚሠጥ ጸጋ ነው።

* **የልሳን ጸጋ**:- ከዚህ ቀደም ተምረው ወይም ሰምተው በማያውቁት ቋንቋ፥ መንፈሳዊ ምስጢርን፥በመንፈስ፥ከጌታ ጋር ለመነጋገርና በልሳን የተነገረውን መልዕክት ተርጉመው ለቤተ ክርስቲያን እንዲገልጹ፥ ከምዕመናን ለአንዳንዶች የሚሠጥ ጸጋ ነው፡ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ በልሳን ቢናገሩም በልሳን የሚናገር ሁሉ ግን የመተርጎም ጸጋ አለው ማለት አይደለም።

* **የተአምራት ጸጋ**:- እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ከተፈጥሮ አካሄድና ልማድ ውጭ በሆኑ ድርጊቶች ክብሩን ለመግለጥ ሲሠራ ለሚጠቀምባቸው ምዕመናን የሚሠጥ ጸጋ ነው። ይህም በፈውስ ብቻ አይወሰንም።

* **የፈውስ ጸጋ**:- ይህም ጌታ እንደ በጎ ፈቃዱ ድውዮችን በድንቅ ሲፈውስ መሣሪያ አድርጎ ለሚጠቀምባቸው ምዕመናን የሚሠጥ የፈውስ አገልግሎት ነው።

ማጠቃለያ:-

የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ሆይ፦ ጌታ ከሁለት ሺ ዓመታት በፊት :- "… መከሩስ ብዙ ነው፥ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ እንግዲህ የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑ:" በ ማለት በማቴዎስ ወንጌል 9 ፥ 37-38 ያዘዘንን እናስብ።

ዘመኑ ወደ ፍጻሜ እየተቃረበ ሲሄድ የወንጌል ሠራተኞች እጥረት እየጨመረ ይሄዳል። ብዙ ሰዎች ወንጌልን መስማት ስላለባቸው፥ እያንዳንዱ ምዕመን ጸጋውን ተረድቶ እያሳደገ በሥራ ላይ መሰማራትና ማፍራት አለበት። ከላይ ለማመልከት የተሞከረው፦ የጸጋ ዓይነቶች በርካታና ልዩ ልዩ መሆናቸውን ነው። ይህም እግዚአብሔርን የምናገለግልባቸው መስኮች እጅግ ሰፊ መሆናቸውን በማመልከት ሥራ ፈትነት ምክንያት እንደሌለው ለማሳየት ነው። ለምሳሌ:-መሐንዲስ፥አናፂ፥ ጸሐፊ፥ ሐኪም፥ የዕዳት ሙያተኛ፥ ሙዚቀኛ ወዘተ ሆነው የወንጌልን መስፋፋት እንዲያገለግሉ ፡ ጸጋን የሚቀበሉ ይኖራሉ። እስቲ ስለ ባስልኤልና ኤሊያብ መጽሐፍ የሚለውን ተመልከቱ:- በተለይም ጌታ በልዩ ልዩ የሙያ ትምሕርት የባረካችሁ ምሑራን አስተውሉ !

ከዚያም እግዚአብሔር ሙሴን አለው፤ "እነሆ፤ከይሁዳ ነገድ የሆር የልጅ ልጅ የሆነውን የኡሪን ልጅ ባስልኤልን መርጩዋለሁ። በሁሉም ዐይነት የእጅ ጠበብ ሥራ ብልሃት ፥ ችሎታና ዕውቀት እንዲኖረው የእግዚአብሔርን መንፈስ ሞልቼዋለሁ፤ ይኸውም በወርቅ፥ በብርና በናስ ለሚሠሩት ሥራዎች በጥበብ የተሠሩ ጌጦችን እንዲያበጅ፥ ድንጋዮችን እንዲቆፍርና እንዲጠርብ በእንጨትም ጥርብ እንዲያወጣ፥ሁሉንም ዐይነት የእጅ ጥበብ ሥራዎችን እንዲያከናውን ነው።" ካለ በኋላ:-

"በተጨማሪም ከዳን ነገድ የሆነውን የአሂሳሚክን ልጅ ኤልያብን እንዲረዳው መርጬዋለሁ፤"ይልና "እንዲሁም ያዘዝሁህን ሁሉ ያደርጉ ዘንድ ለእጅ ጥበብ ዐዋቂዎች ሁሉ ብልሃትን ሰጥቻቸዋለሁ፤…" ይላል። (ዘፀአት 31፥1-6) ለአንተ/ቺ የተሰጠው ምን ይሆን? (በእጅህ የያዝኸው ምንድን ነው? አንሣና ሥራበት።)

ወገኔ፤ እግዚአብሔር ከድቅድቅ ጨለማ አውጥቶ ወደሚደነቀው ብርሃኑ የጠራን ቅዱሳን ካሕናት ሆነን በአገልግሎታችን መንግሥቱን እንድናሰፋ እንጂ:-እንድንቦዝን አይደለም:: ጊዜው የሥራ ጊዜ ነው:: እስቲ የተሰጠንን ጸጋ እንመልከት::አናፂነት÷ አስተማሪነት ወይስ አንጥረኛነት? ቤተ ክርስቲያን ማጽዳት ወይስ ደራሲነት? ነቢይነት ወይስ ሐኪምነት? ወንጌላዊነት ወይስ ጠበቃነት÷ ምንድን ነው የያዝነው?

ውድ ቅዱሳን:- በራሳችንም ሆነ በወንድሞችና በእህቶቻችን ውስጥ ጌታ ያስቀመጠውን ጸጋ ልብ አድርገን መመልከትና ማደፋፈር ÷ ችላ የሚባል ነገር አይደለም:: የብዙ ነፍሳት መዳንን የሚወስን ነገር ነው: ምርኮአችንንም የሚወስን ነው::

አገልግሎት ፓስተርነት ወይም ዘማሪነት ብቻ እንዳልሆነና አንዱም አገልግሎት ከሌላው እንደማያንስ ለማመልከት ነው ጥረታችን:: እንዲሁም:- አንድ አማኝ አንድ ብቻ ወይም በርከት ያሉ ልዩ ልዩ ጸጋዎች ሊኖሩት እንደሚችል ይታወቃል:: ከብዙ ዓመታት በፊት አንድ አገልጋይ: ዘጠኝ የጸጋ ስጦታዎች እንደተሰጠው ሲመሰክር ሰምቼአለሁ:: ዕውነትም ያ ወንድም እስከ ዛሬ ድረስ በአገልግሎቱ ፍሬ የሚገለጥ÷ልዩ ልዩ ጸጋዎች እንዳሉት ማየት ይቻላል::

አንተስ÷ ጌታ በውስጥህ ያስቀመጠውን ጸጋ ተረድተሃል? ከተረዳህስ እያሳደግህና እየሠራህበት ነው? ያለህበት ቤተ ክርስቲያን ጸጋህን ለመግለጥና አሳድጎ ለጌታ ክብር ለማዋል ተባባሪነቱ ምን ያክል ነው?አንተ ራስህ የምዕመናንን ጸጋ መገለጥና አድጎ በሥራ ላይ መሰማራት ምን ያክል ትደግፋለህ?

(መንፈሳዊ ስጦታዎችህ ቤተ ክርስቲያንህን ለማሳደግ ሊረዱ ይችላሉ በሚል ርዕስ ሲ ፒተር ዋግነር ከጻፈው መጽሐፍ የተዘጋጀ:: ፒተር ዋግነር÷የቤተ ክርስቲያን ዕድገትን÷ ጸሎትንና መንፈሳዊ ውግያን አስመልክቶ ታዋቂ ሊቅ ናቸው:: እኚሁ ሰው÷ ዓለም አቀፍ የጸሎት ማዕከል የተባለውን ማዕከል የመሠረቱና÷ብዙ መጻሕፍትን የደረሱ ናቸው:: እጅግ ከታወቁት መጻሕፍቶቻቸው መሐከል:- //Churchquake!, Changing Church, Acts of the Holy Spirit// የሚሉት ይገኛሉ::)

# የሕይወት ለዛ

መንፈሳዊ ድንዛዜ ሲመጣና ሕይወት ጉልበት ማጣት ሲጀምር እንዴት ይታወቃል? የሚከተሉት ሦስት ጥያቄዎች ጣዕምና ለዛ ወደ ሞላበት መንፈሳዊ ሕይወት ለመሻገር ወይም ለመመለስ ሊረዱ ይችላሉ::

1ኛ:- በጉባኤ መካከል አመላለክህ ነፃና የተፈታ ነው? በአምልኮ ወቅት እንደ ልብ መዘመር ይሳንሃል? ወይስ መዝሙሮቹ ልብህ ውስጥ ገብተው ከአምላክህ ጋር ያነጋግሩሃል? ከቤተ ክርስቲያን ስትወጣ÷ የስብከቱን አቃቂር ታወጣለህ ወይስ በሰማኸው ቃለ እግዚአብሔር ላይ ታሰላስላለህ?

እንግዲህ ወደ ተቀጣጠለ ሕይወት ለመሻገር መፍትሔ አለ:: እርሱም ዘማሪዎቹን÷ ስብከትንና የቤተ ክርስቲያኑን አመራር መተቸት ሳይሆን ÷ እግዚአብሔርን ወደ ማምለክ ውስጥ መግባት ነው :: እግዚአብሔርን የሚያመልኩት÷ በዕውነትና በመንፈስ ሊያመልኩት ይገባል:: ይህም ማለት ወደ ግራና ቀኝ ማየት ሳይሆን ትኲረትን ሙሉ በሙሉ ወደ ጌታ ማድረግ ነው:: የመዝሙሮችን ቃላት ልብ ማድረግ::የዜማውን ውበት ማስተዋል:: የስብከቱን ቃል÷ ከግል ሕይወትና ኑሮ ጋር ማገናዘብ ወዘተ: እንዲህም ከሆነ አሳብህ ምን ጎደለ÷ምን ተበላሸ ወደሚለው ሃሳብ አይዋዥቅም:: ነገር ግን ጌታን ለማምለክ ሁሉ ነገር እስኪስተካከል ከጠበቅን÷ የሚገባውን አምልኮ ሳንሰጠው ልንቀር ነው::

2ኛ:- ግላዊ አምልኮህ ጥልቀትና ቀጣይነት አለው? ከብዙ ዓመታት በፊት ግላዊ አምልኮን እንድማር ከሚረዳኝ ከአንድ ወንድም ጋር ነበርሁ:: ያም ሰው በዚያን ጊዜ በክፉ መከራ ውስጥ ያልፍ ነበር:: እኔም አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ ቤቱ ስሄድ አላገኘሁትም:: ከዚያም ባለቤቱ:- "ከቢሮው ሳይሆን አይቀርም" አለችኝና ወደዚያው አመራሁ:: በዚያንም ቀን በኃይል ይዘንብ ነበር እኔም ከዚያች እጅግ ትንሽ ቢሮው አጠገብ ስደርስ ጫማዬ በጐርፍ ሞልቶ ነበር::

ወዲያውም እርሱን ከማየቴ አስቀድሞ ዝማሬውን እሰማ ጀመር:: (የዝማሬውም የአማርኛ ተመሳሳይ እንዲህ ነበር::)

አንተ ምንጭ ሆይ ፍለቅ
አባቶች የማሱህ
አለቆች የቆፈሩህ
ነቢያት የተናገሩህ፤
አንተ ምንጭ ሆይ ፍለቅ
እኛም እንረካለን::

ዓይኖቼን ከመስቀልህ አንስቼ
ወዴት እሄዳለሁ አንተን ትቼ?
ወዴት እሄዳለሁ አንተን ትቼ...?

እያለ በአንዲት ሻማ መብራት÷በዚያች ቢሮ በተባለችው÷ትንሽ የሸመል ጐጆ ውስጥ ሆኖ በፍጹም ልቡ ያመልክ ነበር:: እኔም ላቋረጠው ስላልፈለግሁ መምጣቴንም ሳልነግረው: በመጣሁበት ተመልሼ ሄድሁ:: በዚያችም አጭር ጊዜ ውስጥ ከዓመት ሙሉ ትምሕርት የበለጠ ስለ አምልኮ ተምሬ ተመለስሁ:: ለካስ ወዳጄ የማምለክ ኃይሉን ያገኝ የነበረው÷ በግሉ ጌታን በየዕለቱ ከማምለክ ነበር::

3ኛ:- ቀላል ጥያቄ ልጠይቅህ :: ጌታን በትጋት የማታመልክ ከሆንህ÷ ምክንያትህ ምንድን ነው?

እንደ ነቢዩ ኢሳይያስ በድፍረት ወደ ዙፋኑ በዕምነት ቀርበህ፤ ቅዱስ ÷ቅዱስ÷ቅዱስ! እያሉ ከሚያመልኩት መላዕክቱ ድምጽ ጋር ድምጽህን አዋሕደህ ÷ የሚገባውን አምልኮ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር አቅርብ:: እግዚአብሔር አምላካችን እንዲህ ከልብ የሆነ÷ ዕውነተኛ አምልኮአችንን ይፈልጋልና::

ቻርለስ ስዊንዶል:- "አምልኮ÷ ይብራ ! ይብራ !"በሚል ርዕስ ከሰበኩት መልዕክት ለእኛ በሚገባን አኳኋን ተተረጐመ::

# ጌታ ኢየሱስን ማየት

የአሢሢው ቅዱስ ፍራንሲስ የተባሉ ጻድቅ ሰው ነበሩ። እርሳቸውም ምድራዊውን ፍላጎት ትተው፥በዝቀተኛ ኑሮ እግዚአብሔርን ለመከተል በወሰኑበት ጊዜ፥ ልብሳቸውን አውልቀው ሬቁታቸውን ከከተማው ወጥተው ሄዱ።ወዲያውም አንድ ቍምጥና ያጠቃው ሰው በመንገድ ዳር ቆሞ አገኙ ። አልፈውትም ትንሽ ከሄዱ በኋላ፥ልባቸው ስለ ታወከ ወደ ኋላ ተመልሰው፥ቀማጣውን ሰው እቅፍ አድርገውት ፥ የፍቅር ሰላምታ ሰጥተውት፥ መንገዳቸውን ቀጠሉ። ጥቂትም ከተራመዱ በኋላ፥ዘወር ብለው ቢመለከቱ ሰውየው ተሰወረባቸው። እጅግም ተደነቁ ። ስለዚህም ቅዱስ ፍራንሢስ፥ ያ ያቀፉት ሰው ጌታ ኢየሱስ እንደ ነበረ እያመኑ ኖረው እንዳረፉ በታሪካቸው ይነገራል።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በተናቀና በተዋረደ ሥፍራ መገኘት ልማዱ ነው።በልደቱም በበረት ተወልዶአል። በበሽተኞች ዘንድ ይገኛል። በተጨነቁትና በመከራ ውስጥ ባሉት ዘንድ ያዘወትራል። ስለዚህ ኢየሱስን ማየት ቢፈልጉ:- ልባቸው ወደተሰበረ ችግረኞች ይሂዱ።

"... ያለ ዕምነት ደስ ማሰኘት አይቻልም ፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ፥ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና"። ወደ ዕብራውያን 11 ፥ 6

"...እውነት እላችኋለሁ፥ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት..." ማቴዎስ 25፥ 40

ፊላዴልፊያ በተባለው የአሜሪካን ከተማ የሚኖር አንድ ሰው ነበረ። እርሱም አንድ ቀን (ፍሊ ማርኬት) ወደ ተባለ የአሮጌ ዕቃ መሸጫ ገበያ ሄዶ:-አንድ በመስታወት ውስጥ የተደረገ አሮጌ ሥዕል አገኘ። እርሱም የመስታወቱን ጥራዝ (ፍሬም) ስለ ወደደ ለመግዛት ወሰነ። ዋጋውም ሁለት ዶላር ብቻ ስለ ነበረ ሳያቅማማ ገዛው። ሥዕሉም የአንድ አሮጌ ቤተ ክርስቲያን ያረጀና የተበጣጠሰ ሥዕል ነበር።

ሰውየውም ቤቱ እንደ ደረሰ መስታወቱን ለማጽዳት ከፈት ሲያደርገው፥አንድ በሚገባ የተጣጠፈ ወረቀት ከመስታወቱ ውስጥ ወደቀ። እርሱም አንስቶ ገላልጦ ሲመለከተው:- "የአሜሪካን የነፃነት አዋጅ የተባለው" Declaration of Independence ነበር። ይህ ወረቀት ለሽያጭ ቢገኝ ዋጋው እጅግ የከበረ ነው። አዎን በአሮጌ ዕቃ ገበያ ውስጥ የተገኘውና ሰው ሁሉ፥የሁለት ዶላር አሮጌ ሥዕል የመሰለው ወረቀት፥ ታላቅ ዋጋ ያለው ነው። እርሱም በዓይነቱ አንድ መቶ ቅጅ ብቻ የነበረና :- ሐምሌ 4/1776 ዓም የታተመው በፈረንጆች ዘንድ፥ በተለይም በአሜሪካኖች እጅግ ተፈላጊና ውድ የሆነ ሰነድ ነው።

አያችሁ? ዋጋቸው እጅግ ከፍተኛ የሆኑ ተፈላጊ ነገሮች፥ ፈጽሞ በማይጠበቁበት ሥፍራ ሊገኙ ይችላሉ። በአሮጌ ዕቃ ገበያም ሆነ በሕይወትም፥ ይህ ዕውነት ነው።ስለዚህ ማንን እንደምታገለግሉ ስለማታውቁ:- ለበረንዳ አዳሪዎች፥ለበሽተኞች፥ወላጅ ለሌላቸው፥ ከትዳር ለተፈናቀሉትና በመከራ ውስጥ ላሉት ሰዎች ደግነትን ግለጹ። ራሱን ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን በዚያ ብታገኙትስ ምን ይታወቃል?

የጌታ ቃል እጅግ የሚገርም ነው። "ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁ፥ ለእኔ አደረጋችሁ:" ነው ያለው። ስለዚህ ጌታ ኢየሱስን ማየት የሚችል የተጠቁትንና የተጎዱትን ማየት የሚፈቅድ ሰው ነው።

ጌታ ኢየሱስን ለማየት:- ረዳት የሌላቸው ድኾማን ወደሚኖሩበት ይሂዱ :- ራሳቸውን ስለማይችሉ፥ በሚቻልዎት መንገድ ይደግፏቸው። ጌታ ኢየሱስን ለማየት:- ወደ ሆስፒታሎች ይሂዱና ጠያቂ የሌላቸውን በሽተኞች ይጎብኙ። ጌታ ኢየሱስን ለማየት፥ከትዳሩ በመፈናቀሉ የተነሣ ልጆቹ ናፍቀውት፥ ልቡ የተሰበረበትን ሰው አግኝተው ያጽናኑት። አዎን ጌታ ኢየሱስን ለማየት ከፈለጉ:- የዕለት ጉርስና ማደሪያ ሥፍራ ለሌላቸው፥ ቍራሽ እንጀራ ያካፍሉ ። በመጨረሻም ጌታ ኢየሱስን ለማየት፥ወደ ተናቀውና ወደ ተረሳው ጕረቤትዎ ይሂዱ ። ብዙዎች ጌታ ኢየሱስን በቤተ መንግሥት ይጠባበቁት ነበር። ነገር ግን የሰው ልጆች ሁሉ ተስፋ የሆነውን ጌታ ኢየሱስን ያገኙት አስተዋዮች ወደ በረት ነበር የሄዱት። እርሱም የጌቶች ሁሉ ጌታ፥ በቤተ መንግሥት ውስጥ ሲጠባበቁት በረት ውስጥ ሊወለድ ፈቀደ።

"ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን ያሳፍር ዘንድ የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ፤እግዚአብሔር ብርቱዎችን ያሳፍር ዘንድ የዓለምን ደካማ ነገር መረጠ። እግዚአብሔር የተመረጠውን እንደሌለ ለማድረግ፤በዚህ ዓለም ዝቅ ያለውንና የተናቀውን ነገር መረጠ፤ቦታም ያልተሰጠውን ነገር መረጠ፤ ይኸውም ማንም ሰው በእርሱ ፊት እንዳይመካ ነው።"

(1ቆሮንቶስ 1፥27-30 አ/መ/ት)

# የአንድ አባት ታሪክ

አብዛኞቹ አብያተ ክርስቲያናት ዕሑድ ጧት ብቻ ሳይሆን ማታም ዝግጅት አላቸው:: የአንድ ቤተ ክርስቲያን ቄስ:- አንድ ዕሑድ ማታ በነበረ አገልግሎት ወቅት÷ ጥቂት መዝሙሮች ከተዘመሩ በኋላ÷ ቀስ ብሎ ተነሣና ስብከቱን ከማሰማቱ አስቀድ አንድ በዚያን ምሽት እንግዳ ሆነው የተገኙትን አዛውንት ማስተዋወቅ ፈለገ::

ቄሱም እኒህ አዛውንት ከልጅነቱ ጀምሮ የሚያውቃቸውና የሚያከብራቸው የጌታ ባሪያ መሆናቸውን ገልጾ፥በልባቸው ያለውን ማንኛውንም ነገር ለጥቂት ደቂቃ እንዲናገሩ ጋበዛቸውና መድረኩን ለቀቀላቸው::

አዛውንቱም ተነሥተው ወደ መድረኩ ወጡና ሰላምታ ካቀረቡ በኋላ እንዲህ እያሉ መናገር ጀመሩ:-
"ከዕለታት አንድ ቀን አባት፥ልጅና የልጁ ጓደኛ ሆነው በጀልባ ተሳፍረው ፥ ፓሲፍክ ውቂያኖስ ላይ ይቀዝፉ ነበር:: ከዚያም ወደ ወደቡ ሲመለሱ ሲፈልጉ፥ በእነርሱና በወደቡ መካከል የተነሣው አውሎ ነፋስ መንገዳቸውን ጋረደባቸው:: አውሎውም ብርቱ ነበር::ስለዚህም ምንም እንኳ አባትየው በቂ ልምምድ ያለው ቀዛፊ ቢሆንም፥ ጀልባዋን በትክክል ማስኬድ አልተቻለም::ጀልባዋም ሰመጠችና ሦስቱም ተሳፋሪዎች ወደ ባሕር ተወረወሩ::"

ካሉ በኋላ አዛውንቱ ነገራቸውን ቆም አደረጉና፥ ከአድማጮቹ መካከል ሁለት ወጣቶችን አስተዋሉ:: እነርሱም የታሪኩን ፍጻሜ ለመስማት ጉጉት ይታይባቸው ነበር::

አዛውንቱም ንግግራቸውን ቀጠሉና:-"ከዚያም አባትየው፥ለአደጋ ጊዜ የተዘጋጀውን የማምለጫውን ገመድ ያዘና፥ ከልጁና ከልጁ ጓደኛ የማንኛቸውን ነፍስ ማዳን እንዳለበት ውሳኔ ለማድረግ ተገደደ::ይህን ውሳኔ ለማድረግ ከጥቂት ሰኮንዶች በላይ አልነበረውም:: በዚህን ጊዜ ልጁ አማኝ እንደ ሆነና የልጁ ጓደኛ ግን አማኝ እንዳልሆነ ተገዝ አለው:: የልጁም ጓደኛ ቢሞት ወደ ሲዖል እንደሚሄድ አሰበ:: የማዕበሉም ብርታት አሰቃቂ ነበር:: ከዚያም ለልጁ :- ልጄ ሆይ! በጣም እወድሃለሁ፤ ካለው በኋላ:- የማምለጫ ገመዱን ለልጁ ጓደኛ ወረወረ::

የልጁንም ጓደኛ ጐትቶ ወደ ጀልባ ባወጣው ጊዜ ዞር ብሎ ሲመለከት የራሱ ልጅ በማዕበሉ ተወሰዶ ሞተ:: ሬሳውም እንኳ አልተገኘም::"በዚህን ጊዜ ሁለቱ ወጣቶች እየተንጠራሩ የታሪኩን መጨረሻ ለመስማት ተቍነጠነጡ::) አዛውንቱም ቀጠሉና: "አያችሁ:- አባትየው ልጁ ቢሞት ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደሚሄድ ያውቅ ነበር :: የልጁ ጓደኛ ግን:ጌታ ኢየሱስን ገና አምኖ ስላልተቀበለ ፥ ቢሞት ወደ ሲዖል መሄዱ ነበር:: ስለዚህ <u>የልጁን ነፍስ ከማዳን ይልቅ የልጁን ጓደኛ ነፍስ አዳነ:: የራሱንም ልጅ ነፍስ አሳልፎ ሰጠ</u>::

እምላካችን እግዚአብሔርም ለእኛ ያደረገው ታላቅ ፍቅር እንዲሁ ነው:: እኛን ለማዳን አንዲያ ልጁን አሳልፎ ሰጠ:: ስለዚህ እግዚአብሔር ከዘላለም ሞት ሊያወጣችሁ የዘረጋውን የፍቅር ገመድ እንድትቀበሉ አሳስባችኋለሁ:: ዛሬ የእግዚአብሔርን ቃል ስትሰሙ እልኸኞች አትሁኑ::"ብለው አዛውንቱ ሲቀመጡ፥ በሥፍራው ታላቅ ጸጥታ ሆነ::

ከዚያም ቄሱ ተነሥቶ አጭር መልዕክት ከሰበከ በኋላ የደኅንነት ጥሪ አደረገ:: ወዲያውም የቤተ ክርስቲያኑ ሥርዓት እንዳበቃ እነዚያ ሁለቱ ወጣቶች፥ ፈጥነው ወደ አዛውንቱ መጡ:: ከሁለቱ አንዱም በትኅትና ቀረብ አለና:- "በጣም የሚገርም ታሪክ ነው" ሲል መናገሩን ጀመረ:: ቀጠለና "ነገር ግን አንድ አባት፥የልጁ ጓደኛ ገና ለገና ክርስቲያን ይሆናል በሚል ተስፋ ፥ የአንድ ልጁን ነፍስ መሰዋቱን ማመን ያስቸግራል" በማለት ጥርጣሬውን ገለጸ::

ከዚያም አዛውንቱ በእጃቸው ወደ ያዙት መጽሐፍ ቅዱስ በዓይናቸው ጠቀስ እያደረጉ ሲመልሱለት:- "ልጄ እንዳልኸውም ነገሩ ለማመን ያስቸግራል: አሉት::" ከዚያም በመቀጠል"ስለዚህም ጌታዬ እግዚአብሔር አንዲያ ልጁን አሳልፎ ስለ ኃጢአቴ በሰጠ ጊዜ ፥ እንዴት ባለ የልብ ስብራት ውስጥ እንዳለፈ ያሳስበኛል:: የሚያሳዝነው ግን ጌታ እግዚአብሔር፥ ይህን የመሰለ ዋጋ ከፍሎ፥እንዲህም ታግሶ እየጠበቀ፥ሰዎች ግን ስጦታውን ባለመቀበል ፥ ወደ ሲዖል ሊሄዱ መቻላቸው ነው::" በማለት አስረዱአቸው::

ወዳጄ፥ ያገሬ ሰው ሆይ ! መቼም ለሰው አንድ ጊዜ መሞት ተመድቦአልና፥ ዛሬ ወይም ነገ ነፍስህ ከዚህ ዐለም በሞት ብትለይ፥ወዴት ይሆን የምትሄደው? ወደ ዘላለም ሕይወት ወይስ ወደ ዘላለም ፍርድ? ምርጫህ/ሽን ወስንሃ/ሻል? ውሳኔ ለማድረግ አሁን ጊዜው ነው:: ሕይወትን መምረጥ ይቻላል:: እርሱም የተሰቀለውን ኢየሱስ ክርስቶስን አምኖ በትምሕርቱ ለመኖር መወሰን ነው:: ምክንያቱም:-

<u>"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንዲያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና ፤ እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም የላከው በዓለም ለመፍረድ ሳይሆን፥ ዓለምን በእርሱ ለማዳን ነው:: በእርሱ የሚያምን ሁሉ አይፈረድበትም፤ በእርሱ የማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ፥ አሁኑኑ ተፈርዶበታል::</u> የዮሐንስ ወንጌል 3፥16-18

<u>*የንስሐ ፀሎት*</u>

*ጌታዬ እግዚአብሔር ሆይ! እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ:: እንዳይፈረድብኝ፥ልጅህን ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታዬና መድኃኒቴ ብዬ፥ በዕምነት እቀበላለሁ:: ከእርሱም ሌላ አዳኝ አልሻም፤ መጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርት መሠረት ኑሮዬን ለመኖር ወስኜአለሁ:: ስለዚህ የመንግሥተ ሰማይ ዜጋ አድርገህ ተቀበለኝ:: ስለ ስምህ:: አሜን::*

ቃልህን አክባሪ ቅዱስ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ! ይህንን የንስሐ ፀሎት ከልብ በዕውነት የፀለዩትን ሁሉ፥ ኃጢአታቸውን ይቅር ብለህ ፥ ወደ መንግሥተ ሰማይ ስለ ተቀበልሃቸው ስምህ ይቀደስ ፤ ተመስገን:: ጌታ ሆይ! እኛም ከቅዱሳን መላዕክትህ ጋራ በዕምነት ሐሴት እናደርጋለን:: ጌታ ኢየሱስ ሆይ! ይህንን ዕድል የሰጠኸን አንተ ስለ ሆንህ ፥ ክብር ሁሉ ለቅዱስ ስምህ ይሁን:: አሜን::

በእግዚአብሔር ቃል መሠረት:- የንስሐ ፀሎት በዕምነት የፀለያችሁ ሁሉ:- ጌታ ኃጢአታችሁን ይቅር ብሎአችኋል:: ነገር ግን በጽድቅና በቅድስና ማደግና መኖር ይኖርባችኋል:: ለዚሁም የሚያስፈልጋችሁ ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ማጥናትና ከአማኞች ጋር ሕብረት ማድረግ ነው:: በዚህም እንድንረዳችሁ፥ በሚከተለው ጻፉልን::

በፖስታ:-

God's Love
P.O.Box 6734
Lee's Summit MO 64064 USA

ወይም በኢ-ደብዳቤ e-mail

glnlm@ethiogodslove.org

## እንተርኔት ካለዎት?

ልዩ ልዩ መልዕክቶችን በአማሪኛ አንብቦ ለመታነጽና ምርጥ መንፈሳዊ መዝሙሮችን በማዳመጥ እንዲባረኩ፥የድር ገጽ አገልግሎታችንን በሚከተለው አድራሻ ይጐብኙ::

www.ethiogodslove.org

# ምስጋና

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወዳጆች:- ወንድም ጴጥሮ ክንጉሬ ከፊሰምት ሙዚሬ፥ ቢል የተባለ ሚሲዮናዊ ወንድም ከካሱሓን ሙዚሬ፥ እንዲሁም ተማሪ ረድዔት፥ ከስፕሪንግ ፊልድ ሙዚሬ፥ ያሳፈውን መልዕክታችንን ወጪ ስለ ሸፈናችሁ ሁሉን ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ::

ወንድማችን ሰለሞን በቀለ ከካንሳስ፥ የዚህን መልዕክት ወጪ በመሸፈን ስላደረግህልን ቸርነት፥ የአገልግሎቱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያስፈልግህና በምትጸልይበት ጉዳይህ ያስብህ:: ጌታ ይባርክህ::

# የፀሎት ጥያቄ

በመላው ዓለም በሚሰበከው ወንጌል የብዙ ሰዎች ልብ እንዲነካና ከሚመጣው የጌታችን ቍጣ ብዙዎች እንዲድኑ ዘወትር በፀሎት እንትጋ::

በዚህ የጽሑፍ አገልግሎት፥ በእንተርኔትና በምናመልክበት ቤተ ክርስቲያን የጌታን መንግሥት በትጋት የምናገለግልበት ጸጋ እንዲበዛልን የቅዱሳን ፀሎት ያስፈልገናል:: በተለይም የአገልግሎታችን ፍሬ የሚታያችሁና የሚባርካችሁ ቅዱሳን በቋሚ ፀሎት ሸክማችንን እንድትካፈሉን በጌታ ስም እንጠይቃችኋለን:: <u>ጌታ በልባችሁ በሚያሳስባችሁ ሁሉ</u>፥ <u>በምክር</u>፥ <u>በገንዘብ</u> ሆነ <u>በመልዕክት አስተዋጽዖ ደግፉን</u>:: መከሩ ብዙ ነው ፡ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸውና:- ተባብረን ሠራተኞች እንሁን::

*በእሚግሬሽን ጉዳይ ወደ ጌታ የሚፀልዩትን ወንድሞችና እህቶቻችንን በፀሎት እንተባበራቸው። የቅዱሳን ፀሎት በኃይል ታላቅ ነገርን ታደርጋለችና።*

*ምዕመናን ሁሉ በነፍስ ወከፍ የሚድኑትን ነፍሳት፥ፍሬ ለማምጣት እንድንነሣሣ እንፀልይ። ጸጋው የበዛልን ደግሞ በጾም የተደገፈ ፀሎት እናድርግ። ጊዜው ከቀኑ 11:30 ሰዓት ሆኗል። ሊመሽና፥ ማንም ሊሠራ የማይችልበት ሰዓት ቀርቧል ና ለሥራ እንነሣ። ከጐረቤቶቻችን ወደ ሲዖል የሚወርድ ሰው አይኑር።*

# የሕፃናት ገፅ አገልግሎት

የሕፃናት ገፅ አገልግሎታችን ተጠቃሚዎች ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ ነው:: ለምሳሌ:- <u>በሐምሌ ወር 1129፥ከ39 ሐገሮች</u>፤<u>በነሐሴ ወር 1288 ከ48 ሐገሮች</u> በመስከረም ደግሞ፥በቀን 44 በወሩ 1244 ጊዜ፥ከብዙዎች ከመላው ዓለም ተገልግለዋል:: ክብሩ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ይሁን::

## ኢየሱስ ጌታ ነው::
## ጌታ ይባርካችሁ::